# የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር 46/99ን ለማሻሻል የወጣ

# መመሪያ ቁጥር 87/2005

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን

ሚያዝያ 2005 ዓ.ም

አዲስ አበባ

**<u>የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር 46/99ን ለማሻሻል የወጣ መመሪያ ቁጥር 87/2005</u>**

የግብር ከፋዮችን ችግር በጥናት ለይቶ በየጊዜው የማሻሻያ እርምጃ በመውሰድ ቀልጣፋና፡ ፍትሀዊ አገልግሎት በመስጠት የባለስልጠኑን አሰራር ምቹና ችግር ፈቺ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

ከግብር ከፋዮች ጋር በሚደረጉ የጋራ የምክክር ስብሰባዎች እንደ ችግር ከሚቀርቡ ጉዳዮች በየቀኑ ሽያጭ የሚፈጽሙትም ሆነ የማይፈጽሙት በአንድ ላይ በየቀኑ ዜድ ሪፖርት እንዲያደርጉ በመመሪያ መደንገጉ አግባብ እንዳልሆነ ሲነሳ የቆየ በመሆኑ፣

በየዕለቱ ግብይት የሚፈጽሙትንም የማይፈጽሙትንም ግብር ከፋዮች በአንድ ላይ በየቀኑ ሪፖርት እንዲያደርጉ መመሪያ ቁጥር 46/99 እንደተሻሻለ አንቀጽ 24 ላይ መደንገጉ ከጊዜ፣ ከወጪና ከሰው ሃይል አንጻር በግብር ከፋዮች ላይ ጫና መፈጠሩ በጥናት በመረጋገጡ፣

አቅራቢዎች የሽያጭ መመዝገቢያ ነቁጣ ሶፍትዌር ለደንበኞቻቸው ሲያቀርቡ የሚከተሉትን አፈጻጸም በተመለከተ መመሪያ ቁጥር 51/2000 ወጥቶ የነበረ ቢሆንም ለአፈጻጸም እንዲመች ማሻሻያዎችን አጠቃሎ ማውጣት የተሻለ መሆኑ ስለታመነበት፣

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በዐዋጅ ቁጥር 587/2000 አንቀጽ 6/1/ እና በሽያጭ መሳሪያዎች ስለመጠቀም ግዴታ በወጣው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 139/99 አንቀጽ 22 በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህን የተሻሻለ መመሪያ አውጥቷል፡፡

## 1. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ መመሪያ "የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር 46/99 ለማሻሻል የወጣ መመሪያ ቁጥር 87/2005" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 2.<u>ማሻሻያ</u>

የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎች አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር 46/99 እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡

1) ከአንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 14 ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (15) ተጨምሯል፡፡

"15/ ማናቸውም የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያዎች በተለይም የጥሬ ገንዘብ መመዝገቢያ እና/ወይም የፊስካል ፕሪንተር መሳሪያዎች አቅራቢ መሳሪያዎቹ

ወደ ሀገር ውስጥ ከገቡበት ጊዜ አንስቶ ለአምስት ዓመታት የሚቆይ መለዋወጫ ለማቅረብ ከመሳሪያዎቹ አምራች ጋር የገባውን የዋስተና ውል ለባለስልጣኑ ማቅረብ አለበት፡፡”

2) ከአንቀጽ 9 ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ አንቀጽ 10 ተጨምሯል፡-

“10. <u>የሽያጭ መመዝገቢያ ነቁጣ</u> <u>ሶፍትዌር ሲቀርብ አቅራቢው ሊከተለው ስለሚገባ አፈጻጸም</u>

የሽያጭ መመዝገቢያ ነቁጣ ሶፍትዌር አቅራቢዎች ለደንበኞቻቸው ሶፍትዌር ሲያቀርቡ ቀጥሎ የተመለከቱትን የአፈጻጸም ቅደም ተከተሎች መከተል ይገባቸዋል፡-

1/ የሶፍትዌር ሻጭ የሽያጭ መመዝገቢያ ነቁጣ ሶፍትዌርን ከሽያጭ መመዝገቢያው ነቁጣ መሳሪያ ጋር ወይም ለብቻው ማቅረብ ይችላል፡፡

2/ ማንኛውም የሽያጭ መመዝገቢያ ነቁጣ ሶፍትዌር ሻጭ በባለስልጣኑ ዘንድ ስለ ሶፍትዌሩ አቅራቢነት መመዝገብ እንዲሁም የሚያቀርበውንሶፍትዌር ማስመዝገብ ይኖርበታል፤ ለራሱ የአቅራቢነት፣ ለሚያቀርበውም ሶፍትዌር የምዝገባ ምስክር ወረቀት ሊኖረው ይገባል፡፡

3/ ማንኛውም የሽያጭ መመዝገቢያ ነቁጣ ሶፍትዌር ሻጭ በመመሪያ አንቀጽ 12 ድንጋጌ መሰረት የአቅራቢነት ዕውቅና ለማግኘት የሚያስችለውን የአፈጻጸም ዋስትና ማቅረብ አለበት፡፡

4/ የሽያጭ መመዝገቢያ ነቁጣ ደረሰኝ ዴታ በደንቡ አንቀጽ 7(2) መሰረት በፊስካል ማተሚያ በተቀመጠው የኤሌክትሮኒክ ጆርናል ውስጥ መቀመጥ አለበት፡፡

5/ ማናቸውም የሽያጭ መመዝገቢያ ነቁጣ ሶፍትዌር ከፊስካል ማተሚያ ሌላ ለደረሰኞች ህትመት መፍቀድ የለበትም፡፡

6/ ማናቸውም የሽያጭ ዴታ በኤሌክትሮኒክ ጆርናሉ ከመመዝገቡ በፊት በማንኛውም የኔትወርክ መሳሪያ ወይም ማጠራቀሚያ ላይ መጻፍ የለበትም፡፡

7/ የሽያጭ መመዝገቢያ ነቁጣ ሶፍትዌር ሻጮች የሶፍትዌራቸውን አወቃቀር የጽሁፍና ስዕላዊ መግለጫ ዲዛይን ከሶፍትዌሩ ናሙና በመመሪያው አንቀጽ 13(1) /መ/ እና /ሠ/ መሰረት ሶፍትዌሩን ለማስመዝገብ ማመልከቻ በሚያቀርቡበት ወቅት ለባለስልጣኑ ማቅረብ አለባቸው፡፡

8/ የሽያጭ መመዝገቢያ ነቁጣ ሶፍትዌር ሻጮች የሶፍትዌራቸውን ዓይነት በተገቢው ሁኔታ መጠበቅ የሚገባቸው ሲሆን በአዲስ መልክ የሚለቁትንም ሆነ የማሻሻያ ሶፍትዌር ባለስልጣኑ ሳያውቀው በተጠቃሚዎች መሳሪያዎች ላይ መጫን የለባቸውም፡፡

9/ አዲስ ሶፍትዌር በተለቀቀ ጊዜ የሽያጭ መመዝገቢያ ነቁጣ ሶፍትዌር ሻጮች ስለ ሶፍትዌሩ ተግባራት፣ ከነባሩ ጋር ስለአለው ልዩነትና ለምን ልዩነቶቹ እንደተካተቱ የሚያስረዳ መረጃ ለባለስልጣኑ መስጠት ይጠበቅባቸዋል፡፡

10/ የሽያጭ መመዝገቢያ ነቁጣ ሶፍትዌር፡-

ሀ. የሽያጭ መመዝገቢያ ነቁጣ ማያ የሽያጭ ቁሳቁስን ስሞች ማየትና መምረጥ፣ የባዶ ወይም የመከነ እንዲሁም የተመላሽ አገልግሎቶች ይኖሩታል፤

ለ. እያንዳንዷን የተመዘገበች ሽያጭ በፊስካል ደረሰኝ ያትማል፤

ሐ. እያንዳንዷን የተመዘገበች ባዶ በፊስካል ደረሰኝ ያትማል፤

መ. እያንዳንዷን የተመዘገበች ተመላሽ በፊስካል ደረሰኝ ያትማል፤

ሠ. ማናቸውንም ፊስካል ያልሆኑ ሰነዶች የፊስካል አርማ ወይም የፊስካል አርማ የሚመስል ምልክት በፊስካል ወይም ፊስካል ባልሆነ ማተሚያ እንዳይታተም መከልከል፤

ረ. የፊስካል ማተሚያ ወረቀት በሌለው ጊዜ ወይም ችግር በገጠመው ጊዜ የሽያጭ አገልግሎትን ማቆም፡፡

11/ የሽያጭ መመዝገቢያ ነቁጣ ሶፍትዌር ሻጭ በሶፍትዌሩ ባለ ስህተት ምክንያት ወይም በተገቢው ባልተስተካከለ የሶፍትዌሩ ደህንነት ችግር ምክንያት ለሚፈጠር ያልተገባ ሁኔታ ተጠያቂ ነው፡፡

12/ የሽያጭ መመዝገቢያ ነቁጣ ሶፍትዌር ሻጭ ሶፍትዌሩ የአለውን አገልግሎቶችን የቴክኖሎጂ ገጽታውን እንዲሁም የሚያስፈልገውን የመሳሪያ ፍላጎቶች ተጠቃሚዎች ምርጫ ይኖራቸው ዘንድ አዘጋጅቶ ማሰራጨት ይጠበቅበታል፡፡

13/ የሽያጭ መመዝገቢያ ነቁጣ ሶፍትዌር ሻጭ ለመሳሪያ አምራቾች የሰራው ሶፍትዌር ከሚያመርቷቸው የፊስካል ማተሚያዎች ጋር ይጣጣም እንደሆነ በቂ መረጃ ማቅረብ የሚኖርበት ሲሆን ሶፍትዌሩን ከፊስካል ማተሚያዎች ጋር ለማጣጣም ተገቢውን ሶፍትዌር ማቅረብ አለበት፡፡

14/ የሽያጭ መመዝገቢያ ነቁጣ ሶፍትዌር የካርድ አገልግሎቶችን የሚሰጥ ከሆነ የPayment Card Industry (PCI) Data Security Standards (DSS) guidelines (Payment Application Best Practices) ፍላጎቶች ማሟላት አለበት፡፡ ማናቸውም ሶፍትዌሩ ሻጭ ይህንን ለማሟላቱ ከካርድ አቅራቢው የምስክር ወረቀት ሊሰጠው ይገባል፡፡

15/ የሽያጭ መመዝገቢያ ነቁጣ ሶፍትዌር ሻጭ በባለስልጣኑ የሚዘጋጀውን ደረጃዎችንና የደንበኞችን ፍላጎቶች ለመጠበቁ የማረጋገጫ ጹሁፍ መፈረም አለበት፡፡

3) በመመሪያው አዲስ አንቀጽ 10 በመካተቱ ከአንቀጽ 10 እስከ አንቀጽ 24 የነበሩት አንቀጾች እንደቅደም ተከተላቸው ከአንቀጽ 11 እስከ 25 ሆነዋል፡፡

4) የመመሪያው አንቀጽ 24/1//ረ/ የነበረው በአሁኑ አንቀጽ 25/1/ረ/ በሚከተለው አኳኋን ተሻሽሏል፡፡

ረ. ሽያጭ በየቀኑ የሚያከናወኑ ግብር ከፋዮች የየወቅቱ የሽያጭ ማጠቃለያ ሪፖርት የመጨረሻውን የሽያጭ ደረሰኝ ቁጥር በመያዝ ታትሞ መውጣት የአለበት ሲሆን፤ ወደባለስልጣኑ ሰርቨርም በተርሚናል መሳሪያ በኩል ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዘው አባሪ 1 እና አባሪ 3 መሰረት እየተሞላ መላክ አለበት፡፡

5) ከአንቀጽ 25 ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ አንቀጽ 26 ተጨምሯል*

26. <u>የየወቅቱን ሽያጭ ማጠቃለያ ሪፖርት በየቀኑ ማውጣት</u> <u>ስለማይጠበቅባቸው የንግድ መስኮች፡</u>

1) ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ 4(አራት) ዝርዝራቸው የተገለጹ የሥራ ዘርፎች ላይ የተሰማሩ የተጨማሪ እሴት ታክስ ወይም የተርንኦቨር ታክስ ከፋዮች ሽያጭ በተከናወነ ቁጥር የሚወጣው ዜድ ሪፖርት /z-report/ እንደተጠበቀ ሆኖ፤ ታክሱን ሲያሳውቁ የወሩን የመጀመሪያው ቀንና የወሩን የመጨረሻ ቀን የየወቅቱን ሽያጭ ማጠቃለያ ሪፖርት በማውጣት ከማስታወቂያ ቅጹ ጋር ግብር ለመክፈል በተመዘገቡበት ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ተያይዞ መቅረብ አለበት፣

2) የወሩ የመጨረሻ ቀን ሥራ በማይሰራበት የእረፍት ወይም የሕዝብ በዓላት ቀን ላይ የሚውል በሆነ ጊዜ ዜድ ሪፖርቱ አስቀድሞ ባለው የሥራ ቀን መውጣት አለበት፡፡

3) በሠንጠረዥ 4(አራት) ዋና ዘርፍ&ዘርፍ&ዋና ክፍል&ክፍል ወይም ንዑስ ክፍል በሚል የተመለከቱት ዝርዝራቸውና አፈጻጸማቸው በንግድ ሚኒስቴር በጥር 30 ቀን 2003 ዓ.ም በቁጥር 01.1.18/90 ለባለሥልጣኑ በተላከው የኢትዮጵያ የንግድ ሥራ ፈቃድ መደቦች መመሪያ መሠረት የሚፈጸም ይሆናል፣

4) የታክስ መረጃ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት በየቀኑ ሪፖርት ማውጣት የማይጠበቅባቸውን የንግድ መስኮች ቁጥጥር የማድረግ፣ የመደገፍ፣ ከቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች ጋር በመመካከርና በመተባበር እያጠና የማቅረብና የማስወሰን፣ የሪፖርት አደራረግ ስርዓት የመዘርጋት ስልጣን ተሰጥቶታል፣

5) በዚህ መመሪያ በተገለጸው አግባብ የየወቅቱን የሽያጭ ማጠቃለያ ሪፖርት ወቅቱን ጠብቆ የማያወጣ እና ከታክስ ማስታወቂያ ቅጽ ጋር አያይዞ የማያቀርብ ግብር ከፋይ ወይም የመሳሪያ ተጠቃሚ በግብርና ታክስ ህጎች እና ሌሎች አግባብነት ባላቸው ህጎች በወንጀል ተጠያቂ ይሆናል፣

6) ከአንቀጽ 26 እስከ አንቀጽ 36 የነበሩት አንቀጾች እንደ ቅደምተከተላቸው ከአንቀጽ 27 እስከ አንቀጽ 37 ሆነዋል፡፡

## 3. የተሻሩ መመሪያዎች

የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ አጠቃቀምን በሚመለከት የወጣውን መመሪያ ቁጥር 46/1999/ለማሻሻል/ የወጣ መመሪያ ቁጥር 51/2000 በዚህ መመሪያ ተሸሯል፡፡

## 4. የተሻሻለው መመሪያ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ የተሻሻለ መመሪያ በዋና ዳይሬክተር ተፈርሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ-------------------2005 ዓ.ም

መላኩ ፈንታ

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን

ዋና ዳይሬክተር